# ማርያም ድንግል ንጽሕት

ማርያም ድንግል ንጽሕት ምልዕተ ፀጋ ደስ ይበልሽ (2X)
እመቤቴ እመቤቴ ፊትሽ ወድቄ ልሳለምሽ (2X) } **አዝማች…**

የቆምሽበትን አከብራለሁ በሥዕልሽ ፊት እሰግዳለሁ
ነፍሴ እንድትነፃ ከበደል ዘወትር ከፊትሽ እማልላለሁ
ግዞተኛ ነኝ በዓለም ነፃነቴ ነሽ ማርያም (2X)

**አዝማች…**

የሐሴቦን ልዑል ከሩቅ የጢሮስ ልጆች ከምሥራቅ
መጡ ገስግሰው በደስታ እናትነትሽን ለማድነቅ
አምኃ ይዤ ለብርሽ እኔም ቆሜአለሁ ከደጅሽ (2X)

**አዝማች…**

አስጨናቂዎች ተሸንፈው ስለሚወድቁ ከጫማሽ
የታጠቁትን ሰይፍ ጥለው ማሪን አስምሪን የሚሉሽ
ልቤ ዘለለ በሀሴት ስምሽ ሲጠራ በጸሎት (2X)

**አዝማች…**

አጋንንት ፈሩ በሞገሷ ልታማልደን ስትነሳ
እፁብ ነው ፍቅሯ በረከቷ የዓለምን ፍቅር የሚያስረሳ
ስምሽ ይጠራል ለትውልድ ዘወትር ይኖራል ሲያማልድ (2X)

**አዝማች…**

# አምላክ በአንቺ አደረ

አምላክ በአንቺ አደረ ንፅህናሽን ወዶ (2X)
ከሥጋሽም ሥጋ ከነፍስሽ ነፍስ ወስዶ (2X) } **አዝማች…**

ድንግል እመቤቴ የአምላክ እናት
ተስፋችን ነሽ አንቺ የመግቢያ ገነት
ትንቢት በነቢያት የተነገረልሽ
የኖኅ መርከብ ማርያም ንጽሕት አንቺ ነሽ

**አዝማች…**

የሰሎሞን መቅደስ የሙሴ ጽላት
ከአንቺ ተገኘልን የዓለም መድኃኒት
በክብር ምሥጋና እናመሰግንሽ
አምባ መጠጊያችን ድንግል አንቺ ነሽ

**አዝማች…**

እናምናለን እኛ በእናትነትሽ
ድንግል ሆይ አማልጂን ከቸሩ ልጅሽ
አምላክ በአንቺ አደረ ንፅህናሽን አይቶ
ማደርያ እንድትሆኝው ከፍጥረቱ መርጦ

**አዝማች…**

ድንግል ሆይ ስለ አንቺ ነውና መሐሪ
አማልጂን ከልጅሽ ከቸሩ ፈጣሪ
የኃጥኣን ተስፋ ነሽ ድንግል ዘለዓለም
የክርስቶስ እናት የመድኃኔዓለም

**አዝማች…**

የምትለግሽን ለእኛ በረከት
እስቲ እናመስግንሽ ቅድስት እመቤት
ምሥጋና ይገባሻል እልልታ ዝማሬ
የተቀደሰ ነው የማህፀንሽ ፍሬ (3X)

**አዝማች…**

# ነፍሴ ለእግዚአብሔር

ነፍሴ ለእግዚአብሔር ትዘምራለች
ቸር ፈጣሪዬን ታከብረዋለች
ቅዱስ ነውና ቅዱስ እያለች
ከፍ ያለ ስሙን እያከበረች
} **አዝማች...**

ለረዳኝ አምላክ ደስ እያለኝ
በኃዘኔ ሰዓት ላልተለየኝ
ከነኃጢአቴ ለወደደኝ
የምመልሰው ምንም የለኝ

**አዝማች...**

አስተማሪዬ በኑሮዬ ሁሉ
የሚመዝነኝ በቅዱስ ቃሉ
መንገድ መሪዬ ለእውርነቴ
በእርሱ ተተካ ብቸኝነቴ

**አዝማች...**

በመቅደሱ ፊት ለሚያቆመኝ
ከመሬት ጉድፍ ለሚያነሳኝ
ምንም አላጣሁ ተደግፌህ
ምን ጐደለብኝ ተስፋ አድርጌህ

**አዝማች...**

ለእጆቼ ሰልፍን የሚያስተምር
ታናሽነቴን የሚያከብር
ሰላም ተሞልቷል ቤቴ ጐጆዬ
ይመስገንልኝ ይክበር ጌታዬ

**አዝማች...**

# ይህን ላደረገ ሃሌ ሉያ በሉ

ይህን ላደረገ ሃሌ ሉያ በሉ
እግዚአብሔር ታማኝ ነው ሁልጊዜ በቃሉ
ሙሽራው ሙሽሪት እንኳን ደስ ያላችሁ
የያዕቆብ አምላክ ሞገስ ሆነላችሁ
} **አዝማች...**

ስንቱን ተራራ አልፈነዋል
በሠገነት ላይ አቁሞናል
እስኪ እንዘምር በደስታ
ሁሌ ታማኝ ነው የእኛ ጌታ
ከእኛ የሆነ ምንም የለም
ተመስገን ጌታ ለዘለዓለም
ሥራህ አበራ በምስጋና
በሙሽሮች ላይ እንደገና

**አዝማች...**

የማይሆን መስሎ የታየን
በእግዚአብሔር ሆኖ ስላየን
እንደ አሳፍ ልጆች ተሰልፈን
ስሙን በቅኔ ለማመስገን
የተባረከ በመዳፉ
ቅኔን ያፈሳል ሁሌ በአፉ
ከመላዕክት ጋር አንድ ሆነናል
የእግዚአብሔር ሥራ መስጦናል

**አዝማች...**

ጋኑ ቢጎድል የወይን ጠጁ
ያስባል ጌታ ለወዳጁ
መናኛ ይውጣ ከቤታችን
አዲስ እንጠጣ እርሱን ይዘን
አቤነዘር ነው መዝሙራችን
እየረዳን ነው አምላካችን
ፊታችን በራ በደስታ
ውበት ሆኖናል የእኛ ጌታ

**አዝማች...**

# ማኅደረ መለኮት

ማኅደረ መለኮት
የአምላክ እናት እመቤት
ስምሽን ጠርቶ ያፈረ ማን ነው
የአምላክ እናት ሥራሽ ግሩም ነው } **አዝማች**

ማኅደረ መለኮት .... ደጅሽ ላይ ቆሜ
ማኅደረ መለኮት .... እመብርሃን ነይ ድንግል
ማኅደረ መለኮት ....መፅናኛዬ ነሽ ረዳቴ
ማኅደረ መለኮት .... ጋሻና ጦሬ መከታዬ
ማኅደረ መለኮት .... ስዘምርልሽ ደስ ይለኛል
ማኅደረ መለኮት .... ከልጅሽ ፀጋ ያሰጠኛል

**አዝማች**...

ማኅደረ መለኮት .... አሸብሸቡላት ለድንግል
ማኅደረ መለኮት .... ፍቅሯ ያላችሁ በእውነት
ማኅደረ መለኮት .... ትመጣለች ልትባርከን
ማኅደረ መለኮት .... ድንግል ሆይ ባርኪን ስንላት
ማኅደረ መለኮት .... አፌም ይከፈት ለዝማሬ
ማኅደረ መለኮት .... ለአምላክ እናት ለእመቤቴ

**አዝማች**...

ማኅደረ መለኮት .... ትምክህት ናት ድንግል ለሁሉም
ማኅደረ መለኮት .... ፀዓዳ ብርሕት የሰላም
ማኅደረ መለኮት .... ምን ብዬ ልጥራሽ ላመስግንሽ
ማኅደረ መለኮት .... በምን ምሳሌስ ልመስልሽ
ማኅደረ መለኮት .... ከፍጥረት ሁሉ ነሽ የከበርሽ
ማኅደረ መለኮት .... በንፅሕና የተሸለምሽ

**አዝማች**...

# የቀደሙት አባቶች ምሳሌ

የቀደሙት አባቶች ምሳሌ ያጡልሽ
ቢበዛላቸው ነው በልባቸው ፍቅርሽ
እኛም እንጮሃለን በኤፍሬም ውዳሴ
በአባ ሕርያቆስ ጥዑመ ቅዳሴ } **አዝማች**...

ታቅፈናል በክንድሽ ለዘለዓለም ልጆችሽ ነንና
ዘመርን በደስታ ስለ ፍቅርሽ አንስተን በገና
ሐመልማለ ሲና ተዓምራዊ ደስታን ያየንብሽ
ደስ አላት ነፍሳችን ተደገፋ ቆማ በኪዳንሽ

**አዝማች**...

በቀንና ሌሊት በምስጋና እንጠራሻለን
ቆመናል ማኅሌት ከመቅደስሽ በፍቅርሽ ተማርከን
በረከትሽ ናፍቆን እጃችንን አነሳን ወደ አንቺ
በእናትነትሽ ልጆችሽን ድንግል ተመልከቺ

**አዝማች**...

የዕርገት በር ነሽ ፊደላችን የምንማርብሽ
የአበው ውዳሴ ሞገሳቸው ዘወትር የሚያነሱሽ
ጽድቅን ተምረናል ከሕይወትሽ ግሩም ትሕትና
አግኝተናል ከአንቺ በረከትን የሰማዩን መና

**አዝማች**...

የሕይወታችን ሰላም ምርኩዛችን የደስታ ምንጭ ነሽ
የማትጠፊ ፋና የገነት በር መሰላል አንቺ ነሽ
በስምሽ ተማጽነን የጐደለን አንዳች የለምና
ላንለይ ከከጅሽ ተሰበሰብን ቆምን ለምስጋና

**አዝማች**...

# ሚካኤል አማላጅ ነው

በፍጡራንና ፈጣሪ መካከል
ድርሻ የተሰጠው ሰውን ለማገልገል
ተራዳኢይ መልአክ ጠባቂ የእሥራኤል
የመላእክት አለቃ ስሙ ነው ሚካኤል

አማላጅ ነው ሚካኤል (2X)
የአምላክ ባለሟል
ለነሙሴ ለሕዝበ እሥራኤል
} **አዝማች...**

ፈርኦን በእሥራኤል ላይ በትዕቢት ተነስቶ
ሲከታተላቸው ጦሩን አስከትቶ
ይመራቸው ጀመር ሚካኤል በፋና
ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና

**አዝማች...**

ሙሴ እንደታዘዘው አነሣ በትሩን
እጆቹን ዘረጋ ገሠጸው ባሕሩን
እንደ ግንብ ቆመ ባሕረ ኤርትራ
በደረቅ አለፉ እሥራኤል በተራ

**አዝማች...**

በአፎሚያ ላይ ሲፎክር ጠላት
ፈጥነህ የደረስከው ሊቀ መላእክት
እኛንም ጠብቀን ከክፉ መቅሰፍት
ፈጥነህ ድረስልን ሁነን ረዳት

**አዝማች...**

መልአኩ ሚካኤል አማላጃችን
እንለምንሃለን እንድትጠብቀን
አምላክ በፍርድ ቀን ፃድቃንን ሲጠራ
ዋስ ጠበቃ ሁነን ሚካኤል አደራ

**አዝማች...**

www.ethiopianorthodox.org

# ኢሳይያስ በትንቢት እንደተናገረው

ኢሳይያስ በትንቢት እንደተናገረው
የድንግል ትህትና እጅግ ከፍ ያለ ነው
የዘለዓለም ብርሃን አምላክ ስለሰጣት
ጨረቃም በሌሊት ፀሐይም በመዓልት
<u>አያስፈልጓትም ለእርሷ ሊያበሩላት</u> (2X) } **አዝማች**

ፀሐይ ስትወጣ በድንግል ተወልዶ
ብርሃንን ለብሳለች ፍፁም ተዋኅዶ
በአንቺ ልዩ ፋና እንሄዳለን እንጂ
ድንግል እናታችን የዓለም አማላጅ

**አዝማች . . .**

የዘለዓለም ትምክህት ነሽና ድንግል ሆይ
የልጅ ልጅ ምልክት አርጎሻል አዶናይ
ስምሽ ለዘለዓለም ይወሳል በፍቅር
ይጣፍጣልና ከወተትም ከማር

**አዝማች . . .**

አምላክሽ እግዚአብሔር ብርሃንሽ ነውና
ገጽሽ ለዘለዓለም ይኖራል ሲያበራ
አባቶች በገዳም ፀሐይ አይፈልጉም
ዋሻቸው ያበራል በአዛኝቷ ማርያም

**አዝማች . . .** (2X)

# ማርያም ደስ ይበልሽ

ማርያም ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ
በአንቺ ስላደረ የዓለም ሁሉ ጌታ

የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፎ ሲወጣ ብርሃን

መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሳሪ ገብርኤል ነበረ

ገብርኤል (2X) ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክን መወለድ ሥጋን በመልበስ

በቤተ መቅደስም ተቀምጣ ድንግል
ሐርና ወርቁን አስማምታ ስትፈትል

ገብርኤል ሲያበስራት ድንግል ስትሰማ
በእርሷ ላይ አደረ የመለኮት ግርማ

እውነተኛው ንጉሥ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

# ገብርኤል ኃያል

ገብርኤል ኃያል መልአከ ሰላም መልአከ ብሥራት
የምታወጣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከሚነድ እሳት
ፍቅርህ ተስሏል በልባችን
ፊትህ ቆመናል ባርከን ብለን
} **አዝማች…**

የጽናታቸው ዝናው ሲሰማ
ከዚያች ባቢሎን ከሞት ከተማ
ሕፃናት ሳሉ በራ እምነታቸው
ቆመህ ተገኝህ መሐከላቸው

**አዝማች…**

ውሃው ሲዘልል ቢያስደነግጥም
በጋኖችም ውስጥ ቢነዋወጥም
ጸንተው ዘመሩ ልጅና እናቱ
አንተ ስትደርስ ከዛ ከእሳቱ

**አዝማች…**

ቂርቆስም ጸና ሞትን ሳይፈራ
አንተ ስላለህ ከነሱ ጋራ
አትፍሪ አላት ስለምን ትፍራ
አምነው ድል ነሱ ያንን መከራ

**አዝማች…**

እኔም አምናለሁ አድነኝ ብዬ
ቆመህ አማልደኝ ከቸር ጌታዬ
ክፉውን ዘመን የማልፍበት
ጽናትን ስጠኝ ድል ልንሳበት

**አዝማች…**

# ድንግል በድንግልና

ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ትወልዳለች
ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች } **አዝማች…**

ገና ሳይፀነስ ዘመኑ ሳይገባ
ገረድ መሆን ሻተች ትንቢቱን አንብባ
ልታያት ናፈቀች ያቺን ቅድስት እናት
ለክብሯ ተገዝታ ውኃ ልትቀዳላት
ባርያ ልሁን አለች ዝቅ አድርጋ ራሷን
መች አወቀችና እናቱ መሆኗን
ጥቂት ለሚሻ ሰው ያውቃል ብዙ መስጠት
በማሕፀኗ መቅደስ ሲቀደስ ኖረበት

**አዝማች…**

የዓለም አርነት ጽሕፈት ያለብሽ
የሕይወት ፊደሌ ጽድቅ የተማርኩብሽ
ቢያነቡሽ አታልቂ ምስጢርሽ የሰፋ
ስምሽ ማራኪ ነው ከልብ የማይጠፋ

**አዝማች…**

በሰው ሀገር ስኖር ሰው ጠፍቶ ከጎኔ
ባልንጀራ ሆነሽ የሌሊት ብርሃኔ
ተስፋዬን አብዝተሽ ጥሜን አስታገሽው
በብዙ በረከት ጎጆዬን ሞላሽው

**አዝማች…**

ፍጹም ርኅሩህ ነሽ ስምሽ ጣዕም ያለው
ኃዘኔ ሲበዛ በአንቺ እጽናናለሁ
የዓለም እርካታ የሰላም ውጥን ነሽ
ጊዜ ለጣለው ሰው አይጨክንም ልብሽ

**አዝማች…**

www.ethiopianorthodox.org

# አምላክ ወደደሽ

ከዙፋን ወርዶ ወልደ እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስ
ወደ አንቺ መጣ መረጠሽና ቅዱሱ መንፈስ
ከሴቶች ሁሉ ንፅሕት ሆነሽ ስለተገኘሽ
በማኅጸንሽ አደረ ጌታ አንቺን ወደደሽ

የመልአኩን ቃል እንዳልከው ይሁን በማለትሽ
አምላክ ወደደሽ በአንቺ አደረ በማኅጸንሽ } **አዝማች...**

ያልታሰበውን ስጦታ የሚሰጥ የፍጥረት ጌታ
ሥጋሽን ለብሶ ለአንቺ ሆነልሽ ዕፁብ ስጦታ
ምስጋና ይድረስሽ እንልሻለን እኛ ሁላችን
በአንቺ ምክንያት ስለታደሰ መላ ሕይወታችን

**አዝማች...**

የሔዋን ዕዳ በአንቺ ተካሰ እመቤታችን
የገነትን ደጅ አስከፈትሽልን አስታሪቂያችን
መመኪያችን ነሽ አለኝታችን ነሽ ድንግል ማርያም
ጌታን ያዘልሽው የሚኖረውን በላይ በአርያም

**አዝማች...**

ለዚህ የታደልሽ የምሕረት እናት አማላጃችን
ለኛ ሆንሽልን የሕይወት መሰላል የመዳኛችን
አይጨክን ሆዱ ርኅርህት እናት በአንቺ ተማምነን
በረድኤትሽ እንዳትለይን እንለምንሻለን

**አዝማች...**

# የሚመስልህ የለም

የሚመስልህ የለም የኛ መድኃኔዓለም (2X)
ከፍ በል በዓለም እስከ ዘለዓለም (2X) } አዝማች(2X)

ሰማይና ምድርን በቃልህ አጽንተሃል
እልፍ አእላፋትን መላእክትን ፈጥረሃል
በአፍህ እስትንፋስ ሰውን አኑረሃል
የኛ መድኃኔዓለም ምን ይከፈልሃል (2X)

አዝማች...

የኛን ሥጋ ለብሰህ በምድር ታይተሃል
ኅባጣን አቅንተህ እውር አብርተሃል
ሽባውን ተርትረህ ዲዳን አናግረሃል
የሚሳንህ የለም ሁሉም ይቻልሃል (2X)

አዝማች...

በነፍስም በሥጋም ሰውን ፈውሰሃል
ኅብስቱንም ባርከህ ሁሉን አጥግበሃል
የሠይጣንን ሴራ ኃይሉን አክሽፈሃል
በጨለማ ላሉ ብርሃን ሆነሃል (2X)

አዝማች...

በመስቀል ላይ ሆነህ ሞትንም ሽረሃል
ለሰው ልጆች ሁሉ ትንሣኤን ሰጥተሃል
ወደ ቀድሞ ክብርህ ከፍ ከፍ ብለሃል
በአባትህ ቀኝ ዛሬም ይኸው ተቀምጠሃል
የኛ መድኃኔዓለም ክብር ይገባሃል

አዝማች...(2X)

# ቤተልሔም

<u>ቤተልሔም ቤተልሔም</u> (2X) } **አዝማች**...
ተማርን ከአንቺ ፍቅር ሰላም
ተገኝቶብሽ መድኃኔዓለም

የቃል ኪዳን ምስጢር (ቤተልሔም) የተገለጸብሽ (ቤተልሔም)
ፍጹም ተዋኅዶ « « በእምነት ያየንብሽ « «
የድኅነት ቤታችን « « አንቺ የሰላም ሥፍራ « «
ተገኘ ከአንቺ ዘንድ « « እናድንቅ ይህን ሥራ « «

**አዝማች**...

ትንቢት ተነግሮለት (ቤተልሔም) ኤፍራታ እንደሚያድር (ቤተልሔም)
ስሙም ኃያል አምላክ « « ሊባል ድንቅ መካር « «
የመስቀልን ጉዞ « « ሥራን ሊጀምር « «
ተወለደ አማኑኤል « « ሊያኖረን በክብር « «

**አዝማች**...

ያከበረሽ አምላክ (ቤተልሔም) ፍቅር ያሸነፈው (ቤተልሔም)
ጊዜው ሲደርስ መጥቶ « « ተወስኖ አየነው « «
በአጭር ቁመትና « « በጠባብ ደረት « «
ወርዶ ቢገኝባት « « ምድርን ደነቃት « «

**አዝማች**...

እጅግ ያስገርማል (ቤተልሔም) አምላክ ሰው ሲሆን (ቤተልሔም)
ባክነን ለነበርነው « « ዘመድ ሲያደርገን « «
ምስጋናን አቀረብን « « በሰማይ በምድር « «
ትህትናን ሲያስተምር « « ልጅ ከእናቱ ጋር « «

**አዝማች**...

# በጎል ሰከበ

**በጎል ሰከበ በአጽርቅት ተጠብለለ** (2X)

{**ቤዛኵሉ ዓለም** (2X) **ዮም ተወልደ**} (2X)

**ኧኸ**...

{**ቤዛኵሉ ዓለም** (2X) **ዮም ተወልደ**} (2X)

**በበረት ተኛ በጨርቅ ተጠቀለለ** (2X)

{**የዓለም መድኃኒት** (2X) **ዛሬ ተወለደ**} (2X)

**ኧኸ**...

{**የዓለም መድኃኒት** (2X) **ዛሬ ተወለደ**} (2X)

# ተወለደ

ተወለደ ጌታ ተወለደ
ተወለደ አምላክ ተወለደ } አዝማች…

አንዲት ብላቴና የአሥራ አምስት ዓመት ልጅ
ጌታን ወለደችው በመላእክት አዋጅ
በፍጹም ድንግልና ተወለደ ጌታ
ዓለምን የሚያድን የሰዎች አለኝታ

አዝማች…

ይህ ዓለም በቃሉ ከተፈጠረበት
ይበልጣል ልደቱ አምላክ ሰው የሆነበት
እንደምን ይገርማል ይሄ ተዋኅዶ
አየነው አምላክን እንደ ሰው ተወልዶ

አዝማች…

ፍፁም ድንግልና ክብር የተሞላች
እንደምን አምላክን በማሕፀኗ ያዘች
ዓለምን በቃሉ የፈጠረ ጌታ
ወለደችው ድንግል የሔዋን አለኝታ

አዝማች…

አንቺ ብላቴና እናታችን ማርያም
በምድር ተፈልጐ እንደ አንቺ አልተገኘም
በሃሳብ በግብር ንፁሕ ስለ ሆነች
የአምላክ ማደሪያ ድንግል ተመረጠች

አዝማች…

# አየነው ጌታን አየነው

አየነው ጌታን አየነው
አየነው ወልድን አየነው
ለአባቶቻችን የተገለጠው
በመካከላችን የተመላለሰው
አየነው ጌታን አየነው

**አዝማች…**

የመለኮት ግርማ ክብር መንግሥቱን
ሥጋ ተዋኅዶን ያከበረንን
እኛም አየነው ጌታ ኢየሱስን
በዘመናችን ተገለጠልን

**አዝማች…**

ሽባነታችንን በእጆቹ የፈታ
ዕውር የነበርነው ዓይናችን በራ
ላደረገው ሁሉ ከቶ ምን ልንከፍለው
በደስታ በሐሴት ተመስገን እንበለው

**አዝማች…**

የሲዖል ደጃፍም በእርሱ ሲከፈት
ነፃነት ሲወጡ ነፍሳት ከባርነት
ቅድስና ዛሬ ይኸው ታወጀልን
መድኃኔዓለም ጌታ ተወለደልን

**አዝማች…**

ከአማልዕክት መሐል ማን ይመስልሃል
ፍጥረታት በሙሉ አንተን ያመልኩሃል
በምድር የነበሩ ጻድቃን ሰማዕታት
በሰማይ ዘመሩ ለአምላክ ስብሃት

**አዝማች…**